KA'I QEERRO!!

Sochii Dargaggoota Biyyoolessaa, Bilisummaa fi Dimokraasiif(SDBBD)

National Youth Movement for Freedom and Democracy (NYMFD)

**በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ከወጣቶች ንቅናቄ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ (ቄሮ) የተሰጠ ኣስቸኩዋይ መግለጫ**

የኢትዮጵያ መንግስት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ከዚህ ኣለም በሞት መለየታቸው በመንግስቱ መገናኛ ብዙሃን ኣማካኝነት መታወጁ ይታወቃል። የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሞት ከተሰማ ቢሰነብትም ስርኣቱ ለረጂም ጊዜ ይህንን የመሪውን ዜና እረፍት ደብቆ ኣሁን ገና ማርዳቱ ከመሪው ሞት ጋር ተያያዥ የሆነውን ውስጣዊ ኣለመግባባቶቹን ለማረጋጋት መሆኑን እንገምታለን። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ላለፉት 21 ኣመታት በከንቱ ለጠፋው የሺዎች ህይወት ተጠያቂ ቢሆኑም የኣሟሟታቸው ሁኔታ በተጠበቀው የታሪክ ፍርድ ሳይሆን በመቅረቱና በዜና እረፍቱም እንደ ሰብኣዊነታችንም የተሰማንን ሃዘን እንገልፃለን።

የኣቶ መለስ ዜናዋ ኣስተዳደር ኣምባገነናዊና ፋሺስታዊ ስለመሆኑ ከሳቸው ጋር ኣብረው ሃገር ካደሙት ወገኖች በስተቀር ሌላው ሁሉም ወገን የሚስማማበት ጉዳይ ነው። ኣቶ መለስ ዜናዊ ለፈፀሙት ፋሺስታዊና ኣምባገነናዊ ወንጀሎች ተጠያቂ መሆናቸውን በመጥቀስ ባስቸኩዋይ ስልጣን እንዲለቁ ሚያዝያ 2011 ባወጣነው መግለጫ መጠየቃችን ኣይዘነጋም። በዚህ የቀደመው መግለጫችን ኢትዮጵያ ባለፉት 20 ኣመታት በፖለቲካው፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚው ዘርፍ ለባሰ ቀውስ ኣንደተዳረገች፣ ስርኣቱ የሚመራበት የፖለቲካ ፍልስፍና በስታሊናዊ ፅንሰ ሃሳብ ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ፣ ህግ ደንጋጊው፣ የህግ ዳኛውና ህግ ኣስፈፃሚው የሚባሉት ሶሶቱ ነፃ የመንግስት ኣካላት ያልተለያዩና ነፃነታቸውን ጠብቀው ስራ ላይ እየዋሉ እንዳልሆነና ሌሎችንም ኣንኩዋር ኣንኩዋር ጉድለቶችን በማስታወስ ነበር ጠቅላይ ሚኒስትሩ መለስ ዜናዊ ስልጣን እንዲለቁ የተየቅነው።

ኣሁንም ቀደም ሲል በተጠቀሰው መግለጫ ያነሳነውን ሃሳብ እንደገና ኣፅንኦት በመስጠት የሚከተሉት ጥያቄዎች ኣፋጣኝ ኣዎንታዊ ምላሽ እንዲያገኙ እንጠይቃለን።

1. ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች የብሄር ወይም የሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግባቸው ባስቸኩዋይ ከእስር እንዲፈቱ፣ በተለይም ደግሞ በኣስር ሺዎች የሚቆጠሩትና ኣብዛኞቹ ለ21 ኣመታት ሙሉ እስር ቤት በመሳቀቅ ላይ የሚገኙት የኦሮሞ እስረኞች ባስቸኩዋይ ከእስር እንዲለቀቁ፣
2. ሙስሊሙ ማህበረሰብ ያነሳቸው ጥያቄዎች በኣፋጣኝ ምላሽ እንዲያገኙና በጉዳዩ ጋር በተያያዘ የታሰሩት ኣመራሩም እንዲፈቱ፣
3. "ጸረ ሽብርተኝነት፣ የማህበራዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋዋማት ህግ፣ እና የሚድያ ህግ" በሚል ሽፋን የህዝቦችን የፖለቲካና ማህበራዊ መብቶችን ለማፈን የወጡት ህጎች በኣስቸኩዋይ እንዲነሱ፣
4. ነጻነትና ዴሞክራሲን ለማረጋገጥ ሲባል በህዝቦችና በመንግስት መካከል በተለይም ደግሞ ለህዝቦቻቸው መብት ከሚታገሉ እንደ ኦነግ፣ ኦብነግና በመሳሰሉት ድርጅቶችና በኢህኣዴግ መንግስት መካከል ላለፉት 20 ኣመታት እየተካሄደ የሚገኘው ጦርነት ለህዝብና ለኣለም ማህበረሰብ ግልጽ በሆነ ሰላማዊ ድርድር ፍፃሜ እንዲበጅለት፣
5. በህገ መንግስቱ ውስጥ የተደነገገው የዜጎች ሰላማዊ ሰልፍ የመውጣትና የመሰብሰብ መብት ተግባራዊ እንዲሆንና ይህንን የህዝብ መብት ለማፈን የተጣሉ ገደቦች በሙሉ ባስቸኩዋይ እንዲነሱ፣
6. የመደራጀትና ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መብቶች እንዲከበሩ

የወጣቶች ንቅናቄ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ከላይ የተነሱት ጥያቄዎች ኣስቸኩዋይ ምላሽ እስኪያገኙና ግልጽ የሆነ ለውጥ ገቢራዊ እስከሚሆን ድረስ ትግሉን ኣጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን ያረጋግጣል። ኦሮሞው ህዝባችንና በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ሌሎች የተጨቆኑ

ህዝቦች በሙሉ የነዚህ መብቶች ተጠቃሚ በመሆን ለነጻነትና ለዴሞራሲ የሚያደርጉትን ትግል እንዲያፋፍሙ ጥሪ እናቀርባለን።

ባጠቃላይ የጭቆና ስርኣቱ መዋቅሮች ኣስከሚፈርሱና የህዝቦች የዴሞክራሲ መብቶች እስከሚከበሩ ድረስ የተጀመረው ትግል ተፋፍሞ እንደሚቀጥል በኣፅንኦት ማስገንዘብ እንወዳለን።

ፍትህ ያሸንፋል!

የወጣቶች ንቅናቄ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ (ቄሮ)

ነሃሴ 21, 2012